# የ2026 ዓለም አቀፍ የሜሞሪያል ዴይ መገጣጠም ኮንፈረንስ ቁልፍ መግለጫዎች

ወደ የመለኮታዊው ከፍተኛ ጫፍ በመድረስ፣
የአምላክ-ሰው ኑሮ በመኖር፣
እና በእግዚአብሔር መሠረት መንጋውን ለመንከባከብ
በክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት በመሳተፍ
ይህን ዘመን ወደ ሚያጠናቅቀው ወደ አዲስ መነቃቃት ውስጥ መግባት እንችላለን።

በእግዚአብሔር የተሰጠን የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ
የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መገለጥ –
እግዚአብሔር ሰው የመሆኑና ሰው እግዚአብሔርን የመሆኑ መገለጥ ነው።

ለክርስቶስ አካል መገንባት እና ለአዲስ መነቃቃት፣
የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንደ መንጋው በእረኝነት ለመንከባከብ
ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር መተባበር ያስፈልገናል።

በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ለመንከባከብ፣
ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን፣
በእግዚአብሔር መቀናበር፣ እግዚአብሔርን መግለጥ፣
እግዚአብሔርን መወከል እና እግዚአብሔርን [ለሌሎች] ማገልገል ያስፈልገናል።

*© 2026 Living Stream Ministry*

**የሜሞሪያል ዴይ መገጣጠም ኮንፍረንስ**
**መልእክቶች አውትላይን**
**ግንቦት 14-17፣ 2018**

**አጠቃላይ-ርዕስ፦**
**የአዲስ መነቃቃት ታላቅ አስፈላጊነት**

*መልእክት አንድ*

***ይህንን ዘመን የሚዘጋ አዲስ መነቃቃት ለማምጣት ከጌታ ጋር መተባበር***

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዕን. 3፥2፤ ሐዋ. 26፥19፣ 22፤ ማቴ. 14፥19፣ 22-23፤ ፊልጵ. 1፥19-22፣ 25፤ ዮሐ. 21፥15-17

**I. በእግዚአብሔር ምርጦች መካከል የመነቃቃት ጥብቅ ፍላጎት ሁልጊዜ ነበር—ዕን. 3፥2፤ ሆሴ. 6፥2፤ ሮሜ 8፥20-22፤ መዝ 119፥25፣ 50፣ 107፣ 154፤ ዮሐ. 6፥57፣ 63፤ 2 ቆሮ 3፥3፣ 6።**

**II. በእግዚአብሔር ወደ ተሰጠን ወደ መለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛው ጫፍ—ወደ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መገለጥ (1 ጢሞ. 1፥3-4፤ 1 ቆሮ. 9፥17፤ ሐዋ. 26፥19፣ 22)—በመድረስ ወደ አዲስ መነቃቃት ውስጥ መግባት እንችላለን፤ ይህ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩና የመረጣቸው ሕዝቡን በማደቡ ያለውን ዓላማ በተመለከተ ላለው ታላቁ ጥያቄ ታላቁ መልስ ነው (ዘፍ. 1፥26፤ ኢዮብ 10፥13፤ ተዛ. ኤፌ. 3፥9)፦**

ሀ. በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ የተሰወረው ምሥጢር የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ነው (1፥10፤ 3፥9፤ 1 ጢሞ. 1፥4)፤ ይኸውም የተመረጡት ሕዝቡ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀውን (ራእ. 21፥2—22፥5) ለእግዚአብሔር ሙላት፣ ለእግዚአብሔር መገለጥ የሆነውን (ኤፌ. 1፥22-23፤ 3፥19) ሕይወታዊ አካል፣ እንደ አዲሱ ሰው የክርስቶስ አካል እንዲሆኑ (2፥15-16) እንደ የእርሱ ብዜት ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ይሆኑ ዘንድ (ሮሜ 8፥29፤ 1 ዮሐ. 3፥2) ሕይወታቸውና ባሕርያቸው ለመሆን በመለኮታዊው ሥላሴ እንደ አብ በወልድ ውስጥ በመንፈስ አማካይነት ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን ለማደል ከልብ መሻቱ ጋር የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ውጥን ነው።

ለ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ ለክርስቶስ አካል መፍራትና መገንባት፣ ሰው በሕይወት እና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔርን ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጠ ነገር፣ በመጽሐፍ ቅዱስ "ሳጥን" ውስጥ ያለው "አልማዝ፣" የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ነው—ዘፍ. 1፥26፤ ዮሐ. 12፥24፤ ሮሜ 8፥29፦

1. በተሠግዎ በኩል የሰውን ስብዕና በመካፈል እግዚአብሔር ሰው ሆነ፤ በልውጠት በኩል የእግዚአብሔርን መለኮትነት በመካፈል ተመላኪነቱን ሳይጨምር ሰው በሕይወትና በባሕርይ እግዚአብሔርን ይሆናል—ዮሐ. 1፥14፤ 2 ቆሮ. 3፥18፤ ቆላ. 3፥4፤ 2 ጴጥ. 1፥4፤ ፊልጵ. 2፥5፤ ሮሜ 8፥29፤ ዕብ. 2፥10፤ ኤፌ. 1፥5፤ ሮሜ 8፥19፤ 1 ዮሐ. 3፥2፤ ዮሐ. 1፥12-13።

2. ይህ የመለኮት-ስብዕና የጥንዶች ፍቅር የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ርዕሰ-ጉዳይ፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ይዘትና የመላው አጽናፍ ዓለም ምሥጢር ነው—መኃ. 1፥1፤ 6፥13፤ ተዛ፣ ዕን. 1፥1፤ 2፥4፤ ሮሜ 1፥17፦

   ሀ. ክርስቶስ መለኮትና ሰው ነው፣ የተለወጠችው አፍቃሪውም ሰውና መለኮት ናት፤ አንዳቸው ሌላቸውን ፍጹም በሆነ መንገድ እንዲመጥኑ በሕይወትና በባሕርይ አንድ የሆኑ ናቸው።

   ለ. ባል ለመሆን የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክና ሙሽራይቱን ለመሆን የተለወጠው ሦስት ክፍል ያለው ሰው አንድ ጥንድ፣ ከብዙዎች የሆነ፣ ታላቅ አምላክ-ሰው የሚሆኑ ናቸው—ራእ. 21፥2፣ 9፤ 22፥17።

ሐ. የእግዚአብሔርና የጌታ ምለሳ ማዕከላዊ መገለጥ እግዚአብሔር *ሥጋ* መሆኑ (ዮሐ. 1፥1፣ 14)፣ *ሥጋ* ሕይወትን የሚሰጠው መንፈስ መሆኑ (1 ቆሮ 15፥45) እና የክርስቶስ አካል የምትሆነውንና (ኤፌ. 4፡15-16) አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን የምታጠናቅቀውን (ራእ. 21፥2፣ 9፤ 22፥17፤ ተዛ. ዘፍ. 2፥22፤ ዮሐ. 19፥34) ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት (ማቴ. 16፥18) ሕይወትን የሚሰጠው መንፈስ ሰባት እጥፍ ያየለ መንፈስ መሆኑ ነው (ራእ. 1፥4፤ 3፥1፤ 4፥5፤ 5፥6)።

መ. እግዚአብሔርና ሰው አንድ አካል ይሆናሉ፣ ያም አንድ አካል እንደ መላው መጽሐፍ ቅዱስ መደምደሚያ በአዲሲቱ ኢሩሳሌም የሚጠናቀቀው የመለኮትና የስብዕና መዋሐድ ነው—ራእ. 21፥3፣ 22፣ 2፣ 9፤ ተዛ. ዘሌ. 2፥4-5፤ መዝ. 92፥10።

ሠ. "በምድር ሁሉ ላይ ባሉ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉ ቅዱሳን፣ በተለይም አብሮ ሠራተኞችና ሽማግሌዎች፣ ይህንን መገለጥ እንደሚያዩና እግዚአብሔር አዲስ መነቃቃት—በታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ የማያውቅ መነቃቃት—እንዲሰጠን እንደሚጸልዩ ተስፋ አደርጋለሁ"—*Life-study of 1 and 2 Chronicles*, p. 15።

**III. የክርስቶስ አካል እውነታ የሆነውን የአምላክ-ሰው ኑሮ መኖርን በተግባር የምንለማመድ ከሆነ፣ በቅጽበት ከብዙዎች የሆነ አንድ ሞዴል፣ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖር ሞዴል ይገነባል፤ ይህ ሞዴል ጌታን መልሶ ለማምጣት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ታላቁ መነቃቃት ይሆናል—መዝ. 48፥2 እና የግርጌ ማስታወሻ 1፤ ራእ 3፥12፣ 21፦**

ሀ. በመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ መሠረት ይኖሩ ዘንድ እግዚአብሔር በጸጋው በመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ በኩል ከብዙዎች የሆነ አንድ ሕዝብ እንዲኖሣ ያስፈልገዋል፤ መነቃቃት ያየነው ራእይ ተግባራዊ ልምምድ፣ ተግባራዊነት ነው።

ለ. የክርስቶስ ተከታዮች (ማቴ. 5፥1፤ 28፥19) ደቀ መዛሙርት የተደረጉት እንደ የአምላክ ሰው ሞዴል—በስብዕናው ራሱን በመካድ እግዚአብሔርን በመኖር (ዮሐ. 5፥19፣ 30) ስለ ሰው የነበራቸውን ፅንሰ-ሃሳብ ሥር ነቀል በሆነ መንገድ በመለወጥ (ፊልጵ. 3፥10፤ 1፥21)—በምድር ላይ በነበረው የስብዕና ኑሮ በኩል ነበር።

ሐ. ሕይወታችን የመጀመሪያው አምላክ-ሰው፣ የክርስቶስ ሕይወት ሞዴል ቅጂ፣ መባዛት መሆን አለበት—1 ጴጥ. 2፥21፤ ማቴ. 11፥28-29፤ ኤፌ. 4፥20-21፤ ዮሐ. 17፥4፤ 5፥17፤ ፊልጵ. 1፥19-22፤ 25።

መ. ወደ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ የተተነፈሰው የሕይወትና የእውነታ መንፈስ ከጌታ ጋር ለሦስት ዓመት ተኩል በነበሩበት ጊዜ በእርሱ ወዳስተዋሉት ነገር እውነታ ሁሉ ይመራቸዋል—ዮሐ. 16፥13፤ 20፥22፦

1. በመጀመሪያው አምላክ-ሰው አገልግሎት ጅማሬ ላይ፣ በሥጋው (በስብዕናው—1፥14፤ ሮሜ 1፥3፤ 8፥3) መሠረት ከመሞትና ከመቀበር ውጭ ለምንም እንደማይጠቅም እውቅና በመስጠት ጽድቅን ሁሉ ይፈጽም ዘንድ ተጠመቀ (ማቴ. 3፥5-17)።
2. አምስት ሺ ሕዝብን በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ በመመገቡ ተአምር ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ እንዲማሩ አሰለጠናቸው (11፥29)፤ አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ለመባረክ "ወደ ሰማይ አሻቅቦ" ማየቱ (14፥19) የበረከት ምንጭ እርሱ፣ የተላከው ሳይሆን አብ፣ ላኪው መሆኑን መገንዘቡን ያመለክታል (ዮሐ. 10፥30፤ 5፥19፣ 30፤ 7፥6፣ 8፣ 18)።
3. ጌታ ከሕዝቡ ጋር በተአምሩ ውጤት ውስጥ አልቆየም፣ ነገር ግን በግሉ በጸሎት በተራራ ላይ ከአብ ጋር ይሆን ዘንድ ከእነርሱ ተለይቶ ሄደ—ማቴ. 14፥22-23፤ ሉቃ. 6፥12።
4. ጌታ ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኘትን (ማር. 1፥35፣ ሉቃ. 5፥16፤ 6፥12፤ 9፥28፤ ዕብ. 7፥25)፣ ያለ ማቋረጥ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ የመኖርን (ሐዋ. 10፥38፤ ዮሐ. 8፥29፤ 16፥32) እና ሰዎችን ወደ የእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ኢዩቤልዩ ውስጥ ለማምጣት ከእነርሱ ጋር የመገናኘትን፣ እግዚአብሔርን ወደ እነርሱ ውስጥ የማገልገልን ኑሮ ኖረ (ሉቃ. 4፥18-19፤ ዕብ. 8፥2፤ ተዛ. ዘፍ. 14፥18፤ ሐዋ. 6፥4)።
5. የዚህ ዓለም ገዢ ሰይጣን በእርሱ አንዳች (ምንም ሥፍራ፣ ምንም እድል፣ ምንም ተስፋ፣ በአንድም ነገር ቢሆን ምንም እጣ ፈንታ) የሌለው ሰው ነበር—ዮሐ. 14፥30፤ ተዛ. ቁ. 20፤ 2 ቆሮ. 12፥2፤ ቆላ. 1፥27፤ 2 ጢሞ. 4፥22፤ ዮሐ. 3፥6፤ 4፥23-24፤ 1 ዮሐ. 5፥4፣ 18)።

ሠ. በጌታ ሞዴል መሠረት የአምላክ-ሰው ኑሮ ለመኖር ብቸኛው መንገድ መላው ማንነታችን በተዋሐደው መንፈስ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣ በተዋሐደው መንፈስ መሠረት መመላለስ፣ መኖርና ማንነታችንን ማድረግ ነው—ሮሜ 8፥2፣ 4፣ 10፣ 6፣ 11፣ 16፤ 1 ቆሮ. 6፥17፤ ሮሜ 10፥12፤ ገላ. 5፥25፤ ኤፌ. 6፥17-18፤ 1 ተሰ. 5፥16-20፤ 1 ጢሞ. 4፥6-7፤ 2 ጢሞ. 1፥6-7።

ረ. "ሁላችንም የአምላክ-ሰው ኑሮ መኖር እንፈልጋለን ብለን ማወጅ አለብን፤ በመጨረሻም፣ አምላክ-ሰዎች የሆኑት አሸናፊዎች፣ ድል ነሺዎች፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ ጽዮን ይሆናሉ። ይህ በታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ መነቃቃት ያመጣል፣ ይህም ይህንን ዘመን ይዘጋል"—*Life-study of 1 and 2 Chronicles*, p. 28።

**IV. የእግዚአብሔርን መንጋ፣ እርሷም የክርስቶስን አካል የምታመጣውን ቤተ ክርስቲያንን ለመንከባከብ ጠቦቶቹን እንመግብና በጎቹን በእረኝነት እንንከባከብ ዘንድ በክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ውስጥ በመሳተፍ ወደ አዲስ መነቃቃት ውስጥ መግባት እንችላለን—ዮሐ. 21፥15-17፤ 1 ጴጥ. 2፥25፤ 5፥1-4፤ ዕብ. 13፥20-21፤ ራእ. 1፥12-13፦**

ሀ. ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መከናወን ባለው አገልግሎቱ በጌታ ኢየሱስ ምሳሌ መሠረት ሰዎችን በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—ማቴ. 9፥36፤ ዮሐ. 10፥11፤ ዕብ. 13፥20፤ 1 ጴጥ. 5፥4፦

1. በሙሉ ማዳኑ ውስጥ ያለው የመላው የእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ይዘት ክርስቶስ እንደ የሰው ልጅ በሞቱ ፍትሃዊ ቤዛነትን በመፈጸም እኛን ከኃጢአት በመቤዠት ማስደሰቱ (1 ጢሞ. 1፥15፤ ኤፌ. 1፥7) እና ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ልጅ በትንሣኤው ሕይወታዊ ማዳኑን በማከናወን መለኮታዊ ሕይወቱን አትረፍርፎ ያካፍለን ዘንድ እኛን መመገቡ ነው (ዮሐ. 10፥10፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ ኤፌ. 5፥29)።
2. የአብ አፍቃሪና ይቅር ባይ ልብ የሌለን መሆናችንና የአዳኙ የእረኝነት እንክብካቤና የሚፈልግ መንፈስ የሌለን መሆናችን ለመካንነታችን ምክንያት ናቸው—ሉቃ. 15፥1-24።
3. ሰዎችን በኢየሱስ ስብዕና ማስደሰት (ሰዎችን ደስ ማሰኘትና ደስታና ምቾት እንዲሰማቸው ማድረግ) ያስፈልገናል (ማቴ. 9፥10፤ ሉቃ. 7፥34)፤ ሰዎችን በኢየሱስ መለኮት (ሦስት ደረጃዎች ባለው አገልግሎቱ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ) መመገብ ያስፈልገናል (ማቴ. 24፥45-47)።
4. እንደ የሕይወት ውኃ ወንዝ በሚፈስሰው ሦስታንዱ አምላክ ይመግባት ዘንድ፣ የሚጠጣው ነገር ትሰጠው ዘንድ በመጠየቅ ደስ ሊያሰኛት ክርስቶስ አንዲት ኃጢአተኛን ሴት ለማግኘት ሆን ብሎ መንገዱን ቀይሮ በሲካር በኩል በመዞር በሰማርያ ማለፍ ነበረበት—ዮሐ. 4፥3-14፤ ራእ. 22፥1።
5. ኃጢአት እንደሌለበት ማንነት፣ በፍትሃዊ መንገድ ለኃጢአቶቿ ይቅርታና በሕይወታዊ መንገድ ከኃጢአቶቿ ለመፈታቷ አመንዝራይቱን ሴት ደስ አሰኛት እንጂ አልኮነናትም (ዮሐ. 8፥1-11፣ 32፣ 36)፤ ክርስቶስ በመሰቀሉ በኩል ያዳነው የመጀመሪያው ሰው ሞት የተፈረደበት ወንበዴ መሆኑም እጅግ ትርጉም ያለው ነው (ሉቃ. 23፥42-43)።
6. ጌታ አንድን ሰው፣ የቀራጮች አለቃ የሆነን ሰው ለመጎብኘትና ለማግኘት ብቻ ወደ ኢያሪኮ ሄደ፣ ስብከቱ የእረኝነት እንክብካቤው ነበር (19፥1-10)፤ እጆቹን በልጆቻቸው ላይ በመጫንም ወላጆችን ደስ አሰኝቷል (ማቴ. 19፥13-15)።

ለ. የእግዚአብሔርን መንጋ ለመንካባከብ እንደምታጠባ እናትና እንደ የሚመክር አባት ቅዱሳንን በእረኝነት በተንከባከበው በሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌ መሠረት ሰዎችን በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—1 ተሰ. 2፥7-8፣ 11-12፤ 1 ጢሞ. 1፥16፤ ሐዋ. 20፥28፡-

1. ጳውሎስ በኤፌሶን የነበሩትን ቅዱሳን "በጉባኤና በየቤቱ" (ቁ. 20) በማስተማርና እያንዳንዳቸውን ለሦስት ዓመታት በእንባ በመገሠጽ (ቁ. 31፣ 19)፣ የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ እየነገራቸው (ቁ. 27) በእረኝነት ተንከባከባቸው።
2. ጳውሎስ ለአማኞች የቅርብ ግድ መሰኘት ነበረው (2 ቆሮ. 7፥2-7፤ ፊልሞ. 7፣ 12)፣ ያገኛቸው ዘንድም ወደ ደካሞች ደረጃ ወርዷል (2 ቆሮ. 11፥28-29፤ 1 ቆሮ. 9፥22፤ ተዛ. ማቴ. 12፥20)።
3. ስለ ቅዱሳን ሲል ንብረቱን በማመልከት የነበረውን ሁሉ ለመክፈል፣ ማንነቱን በማመልከት የሆነውን ሁሉ ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር (2 ቆሮ. 12፥15)፤ ጳውሎስ ወይን ከሚያዘጋጀው ክርስቶስ ጋር አንድ የነበረ፣ ለሌሎች የክርስቶስ ድሰታ ራሱን የሚሰዋ የመጠጥ ቁርባን ነበር (ፊልጵ. 2፥17፤ መሳ. 9፥13፤ ኤፌ 3፥2)።
4. ጳውሎስ ሰውን ለማክበር መንፈስን ማገልገል ይችል ዘንድ እግዚአብሔርን ለማክበር በመንፈስ ተመላለሰ—2 ቆሮ. 3፥3፣ 6፣ 8፤ ገላ. 5፥16፣ 25፤ መሳ. 9፥9።
5. ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ለማሳደግ ቤት፣ ለመፈወስና ለመመለስ ሆስፒታል፣ ለማስተማርና ለማነጽ ትምህርት ቤት መሆኗን ጳውሎስ በትምህርቱ አመላክቷል—ኤፌ. 2፥19፤ 1 ተሰ. 5፥14፤ 1 ቆሮ. 14፥31።
6. ለክርስቶስ አካል ግንባታ ምንም ነገር ለመሆናችንና ምንም ነገር ለማድረጋችን ፍቅር እጅግ የላቀው መንገድ እንደሆነ ገልጧል—8፥1፤ 12፥31፤ 13፥4-8፤ ኤፌ. 1፥4፤ 3፥17፤ 4፥2፣ 15-16፤ 5፥2፤ 6፥24፤ ራእ. 2፥4-5፤ ቆላ. 1፥18፤ 1 ተሰ. 1፥3።

ሐ. "ይህንን በእረኝነት የመንከባከብ ሸክምን በመቀበላችን በመካከላችን እውነተኛ መነቃቃት እንደሚኖር ተስፋ አደርጋለሁ። ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በክርስቶስ ድንቅ የእረኝነት እንክብካቤ ይሳተፉ ዘንድ ይህንን ትምህርት ከተቀበሉ፣ በምለሳው ትልቅ መነቃቃት ይኖራል"—*The Collected Works of Witness Lee, 1994–1997,* vol. 5, "The Vital Groups," p. 92.

© 2026 Living Stream Ministry

መልእክት ሁለት

**ወደ መለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛው ጫፍ መድረስ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ጢሞ. 1፥4፤ ኤፌ. 1፥10፤ 3፥9፤ ሮሜ 1፥3-4

**I. በእግዚአብሔር የተሰጠን የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛው ጫፍ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መገለጥ ነው—ሰው በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔርን ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ፦**

ሀ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መብራራት የሆነው መላው መጽሐፍ ቅዱስ በሁለቱ የዘላለም ክፍሎች ውስጥ እና በጊዜ ድልድይ ላይ የሚታየው የሦስታንዱ አምላክ የግል የሕይወት ታሪክ ነው፦

1. ሦስታንዱ አምላክ ከዘላለም ወደ ጊዜ ውስጥ መጣ፣ ፍትሃዊ ቤዛነቱን ለመፈጸም በአራቱ ወንጌላት እንደታየው በሰው ውስጥ ላለው ቀጥተኛ እንቅስቃሴው *ሥጋ* የለበሰው አምላክ ለመሆን ወደ ስብዕና ውስጥ ለመግባት ከመለኮትነቱ ጋር መጣ—ዮሐ. 1፥14፣ 29።
2. ሕይወታዊ ማዳኑን ለማከናወን በሐዋርያት *ሥራ* እና በመልእክቶች የሚታየው በትንሣኤ የተቀመመው አምላክ፣ "በሂደት ያለፈው" አምላክ፣ ሁሉን-ያካተተው ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ—ዮሐ. 1፥32፣ 42፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ ፊልጵ. 1፥19።
3. በወደፊት ዘላለም በራእይ 21 እና 22 የሚታየው ብዙዎች የተካተቱበት አምላክ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይሆናል።
4. በሂደት ያለፈው እና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ዳግም ከተወለዱት፣ ከተለወጡትና ከከበሩት አማኞች ጋር አጽናፍ-ዓለማዊው፣ የመለኮት-ስብዕና መካተት [መሆኑ] የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ ነው—ዮሐ. 1፥51፤ ራእ. 21፥3፣ 22።
5. የእግዚአብሔር እና የጌታ ምለሳ ማዕከላዊ መገለጥ እግዚአብሔር *ሥጋ* መሆኑ፣ *ሥጋ* ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ መሆኑ እና የክርስቶስ አካል የምትሆነውን እና በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ ሰባት እጥፍ ያየለ መንፈስ መሆኑ ነው።

ለ. ሰው በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔርን ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጠ-ነገር፣ በመጽሐፍ ቅዱስ "ሳጥን" ውስጥ ያለው "አልማዝ"፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ነው—ዘፍ. 1፥26፤ ዮሐ. 12፥24፤ ሮሜ 8፥29፦

1. እግዚአብሔር የሰውን ስብዕና በመካፈል በተሠግዎ በኩል ሰው ሆነ፤ ሰው የእግዚአብሔርን መለኮትነት በመካፈል በልውጠት በኩል እግዚአብሔር ይሆናል፦
   ሀ. የእግዚአብሔርን ሕይወት በመካፈል—ዮሐ. 3፥15፤ ቆላ. 3፥4።
   ለ. የእግዚአብሔርን ባሕርይ በመካፈል—ኤፌ. 1፥4፤ 2 ጴጥ. 1፥4።
   ሐ. የእግዚአብሔርን አእምሮ በመካፈል—ኤፌ. 4፥23፤ ፊልጵ. 2፥5።
   መ. የእግዚአብሔርን ማንነት በመካፈል—2 ቆሮ. 3፥18፤ ኤፌ. 3፥8።
   ሠ. የእግዚአብሔርን መልክ በመካፈል—2 ቆሮ. 3፥18፤ ሮሜ 8፥29።
   ረ. የእግዚአብሔርን ክብር በመካፈል—ቁ. 30፤ ዕብ. 2፥10።
   ሰ. የእግዚአብሔርን ልጅነት በመካፈል—ኤፌ. 1፥5፤ ሮሜ 8፥23።
   ሸ. የእግዚአብሔርን መገለጥ በመካፈል—ቁ. 19።
   ቀ. የእግዚአብሔርን አምሳል ለመያዝ—1 ዮሐ. 3፥2።
   በ. የእግዚአብሔር ወገን—የእግዚአብሔር ዝርያ ለመሆን—ዮሐ. 1፥12፤ ሮሜ 8፥14፣ 16።
2. ይህ የመለኮት-ስብዕና የጥንዶች ፍቅር የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ርዕሰ-ጉዳይ፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ይዘት እና የመላው አጽናፍ-ዓለም ምሥጢር ነው—መኃ. 1፥1፤ 6፥13።

**II. የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ—በመጽሐፍ ቅዱስ "ሳጥን" ውስጥ ያለው "አልማዝ"—ሰው በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሰው የመሆኑ መገለጥ ነው—2 ሳሙ. 7፥12-14፤ ሮሜ 1፥3-4፤ ኤፌ. 3፥17፦**

ሀ. "እግዚአብሔር ሰው መሆኑ እና ሰው እግዚአብሔርን መሆኑ" የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ነው—1 ጢሞ. 1፥4

ለ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ እግዚአብሔር በመገለጡ ይተልቅና ይሰፋፋ ዘንድ መለኮታዊ ባሕርያቱ ሁሉ በሰው ሰናይ ባሕርያት እንዲገለጡ በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ሰውን ልክ እንደ ራሱ ማድረግ እና ራሱን ከሰው ጋር አንድ ማድረግ፣ ሰውንም ከራሱ ጋር አንድ ማድረግ ነው—ኤፌ. 3፥9፤ 1፥10፦

1. የእግዚአብሔር በጎ ደስታ ከሰው ጋር አንድ መሆንና ሰውን በሕይወትና በባሕሪይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ከራሱ ጋር አንድ ዓይነት ማድረግ ነው—ቁ. 5፣ 9።
2. እግዚአብሔር የራሱ ብዙ ርቢ እንዲኖረውና በዚህም አዲስን ወገን—አምላክ-ሰው ወገን—ለማፍራት ሰው ሆነ—ዮሐ. 1፥1፣ 14፤ 12፥24።

ሐ. ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም፣ እኛን በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ለማድረግ እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ እንደ ሕይወታችን፣ ባሕርያችን እና ቅንብራችን ወደ ውስጣችን እንዲገነባ ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፥17፤ ቆላ፣ 3፥4፣ 10-11።

መ. እግዚአብሔር በተሠግዎ ሰው ሆነ፤ ሰው ዳግም በመወለድ፣ በመቀደስ፣ በመታደስ፣ በልውጠት፣ በመምሰል እና በመከበር እግዚአብሔርን ይሆናል—ዮሐ. 3፥5-6፤ 1፥12-13፤ ሮሜ 6፥19፣ 22፤ 12፥2፤ 8፥29-30።

**III. የክርስቶስ አካል መፍራት የሚችለው ሰውን እግዚአብሔር ለማድረግ እግዚአብሔር ሰው በመሆኑ ብቻ ነው፤ ይህ ነጥብ በእግዚአብሔር የተሰጠን ራእይ ከፍተኛው ጫፍ ነው—ቁ. 3፤ 1፥3-4፤ 8፥14፤ 12፥4-5፦**

ሀ. የክርስቶስን አካል—ከፍተኛና የመጨረሻ መገለጧ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሆነችውን የሦስታንዱን አምላክ ሕይወታዊ አካል—ያፈራ ዘንድ ሰውን እግዚአብሔር ለማድረግ እግዚአብሔር ሰው ሆነ—ኤፌ. 1፥22-23፤ 4፥4-6፤ ራእ. 21፥2፣ 9-10።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የአምላክ-ሰው ኑሮ እንዲኖረው እንዴት እግዚአብሔርን መሆን እንደሚችል እና ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ሕይወታዊ አካል እንደሚሆን ያሳየናል—ሮሜ 1፥3-4፤ 12፥4-5፦

1. ይህ ሕይወታዊ አካል እግዚአብሔር ሰውን እግዚአብሔር ለማድረግ ራሱን ከሰው ጋር ማጋጠሙና ማዋሐዱ ነው።
2. እግዚአብሔር ሰው የመሆኑ እና ሰው እግዚአብሔር የመሆኑ ውጤት ሕይወታዊ አካል ነው፤ ይህ ሕይወታዊ አካል የክርስቶስ አካል—የእግዚአብሔር ከሰው ጋር መጣመርና መዋሐድ ነው—ኤፌ. 4፥4-6፣ 12።

ሐ. እግዚአብሔር ልጁን የላከው ሰው እንዲሆንና በመለኮታዊው ሕይወት የአምላክ-ሰው ኑሮ እንዲኖር ነው፤ እንዲህ ያለው ኑሮ ከእርሱ ጋር ቁርጥ አንድ ዓይነት የሆነን አጽናፍ ዓለማዊ ሰውን—በመለኮታዊው ሕይወት የአምላክ-ሰው ኑሮ የሚኖር ከብዙዎች የሆነ አንድን ሰው ያመጣል—ሮሜ 8፥3፤ 12፥4-5።

መ. የክርስቶስ አካል እውነታ ከብዙዎች የሆነ አምላክ-ሰው በኑሮ እንዲገለጥ የእግዚአብሔር ከሰው ጋር መጣመርና መዋሐድ ነው—ኤፌ. 4፥4-6፣ 24።

© 2026 Living Stream Ministry

መልእክት ሦስት

**ለአዲስ መነቃቃት የአምላክ-ሰው ኑሮ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘሌ. 1፥3፤ 9፤ 6፥8-13፤ ዮሐ. 21፥15-17፤
1 ዮሐ. 3፥14፤ 5፥1፤ 2፥6፤ 4፥17፤ ገላ. 6፥2-3፤ ሮሜ 8፥2

**I. የእግዚአብሔር የልብ መሻት፣ ለአዲስ መነቃቃት በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛው ጫፍ የሆነው የክርስቶስ አካል እውነታ (ኤፌ. 4፥20-24) ይሆኑ ዘንድ፣ "እውነት በኢየሱስ እንዳለ" (ቁ. 21)፣ በአራቱ ወንጌላት የተዘገበው እውነተኛው የኢየሱስ የአምላክ-ሰው ኑሮ፣ በእውነታ መንፈስ ወደ ብዙዎቹ የክርስቶስ አካል ብልቶች ውስጥ እንዲባዛ ነው፦**

ሀ. አራቱ ወንጌላት እግዚአብሔር የሚሻውን ኑሮ ምሳሌ፣ እግዚአብሔርን ማርካት እና ዓላማውን መፈጸም የሚችለውን ኑሮ ቅርጽ ማስያዣ ያሳያሉ፤ ኢየሱስ ሁሉን ነገር በእግዚአብሔር ውስጥ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እና ለእግዚአብሔር ያደረገበትን ኑሮ ኖረ፤ እግዚአብሔር በኑሮው ውስጥ ነበር፣ ከእግዚአብሔርም ጋር አንድ ነበር፤ *እውነታ በኢየሱስ አለ* ማለት ይህ ነው፤ እውነታ በኢየሱስ እንዳለ ክርስቶስን መማር በክርስቶስ ምሳሌ ውስጥ ቅርጽ መያዝ፣ የክርስቶስን መልክ መምሰል ነው—ሮሜ 8፥28-29፤ ኤፌ. 4፥20-21።

ለ. እንደ የመጀመሪያው አምላክ-ሰው በክርስቶስ ሞዴል መሠረት ተፈጥሯዊ ሕይወታችንን በመካድ መለኮታዊውን ሕይወት በመኖር አምላክ-ሰዎች እንሆን ዘንድ በጌታ ፍጹም እየተደረግን ነው—ማቴ. 11፥29፤ 17፥5፤ 1 ጴጥ. 2፥21፦

1. በአራቱ ወንጌላት እንደተገለጠው በምድር ላይ በነበረው ሕይወቱ ምሳሌን አስቀመጠ፤ ከዚያም ሕይወታችን ለመሆን ወደ ውስጣችን ይገባ ዘንድ ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ ለመሆን ተሰቀለ፣ ከሞትም ተነሣ፤ በእርሱ ምሳሌ መሠረት፣ በተፈጥሯዊው ሕይወታችን ሳይሆን በትንሣኤ እንደሆነው ሕይወታችን፣ ከእርሱ እንማራለን—1 ቆሮ. 15፥45፤ ቆላ. 3፥4።
2. የክርስትና ሕይወታችን በክርስቶስ ውስጥ ያለ ሕይወት እና በውስጣችን ያለ የክርስቶስ ሕይወት ነው፤ ቅርጽ ማስያዣ በሆነው በክርስቶስ ውስጥ ነን፣ እርሱም እንደ ሕይወታችን በውስጣችን ነው፤ በዚህ መንገድ እውነታ በኢየሱስ እንዳለ ክርስቶስን እንማራለን፤ ይህ እውነታ የክርስቶስ አካል እውነታ ነው—1 ቆሮ. 1፥30፤ 2 ቆሮ. 5፥17፤ 12፥2፤ ቆላ. 1፥27፤ ገላ. 2፥20፤ ሮሜ 8፥10።

ሐ. ጌታን ስንወድ፣ እርሱን ስንነካው እና ወደ እርሱ ስንጸልይ፣ በወንጌላት በተገለጸው ቅርጽ ማስያዣ፣ መልክ፣ ምሳሌ መሠረት ኦቶማቲክ በሆነ መንገድ እርሱን እንኖራለን፤ በዚህ መንገድ ወደዚህ ቅርጽ ማስያዣ መልክ እንቀረጻለን፣ የዚህን ቅርጽ መልክ እንመስላለን—ክርስቶስን መማር ማለት ይህ ነው—ማቴ. 11፥29፤ ሮሜ 8፥29።

መ. በተዋሐደው መንፈስ ስንኖር፣ በእውነታ መንፈስ በኢየሱስ ባለው እውነታ መሠረት ክርስቶስን እየተማርን ነው፤ የእርሱ የሕይወት ታሪክ የእኛ ታሪክ ይሆን ዘንድ እንደ ሞዴላችን ከእርሱ እንማራለን፤ እንደ አዲሱ ሰው የክርስቶስ አካል ኑሮ በወንጌላት ከተገለጠው የኢየሱስ ኑሮ ጋር ፍጹም አንድ ዓይነት መሆን አለበት—ገላ. 6፥17-18፤ ሮሜ 1፥1፣ 9፤ ኤፌ. 4፥20-24፤ ፊልጵ. 2፥5፤ ማቴ. 11፥29፤ 1 ጴጥ. 2፥21።

ሠ. ጌታ ኢየሱስን ሰው እንዲሆን በመላኩ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ በመለኮታዊው ሕይወት የአምላክ-ሰው ኑሮ እንዲኖር ነበር፤ እርሱን ስንበላ ፈጽሞ እርሱን የሚመስል አጽናፍ ዓለማዊ ታላቅ ሰው—በመለኮታዊው ሕይወት የአምላክ-ሰውን ኑሮ የሚኖር ሰው—እንሆን ዘንድ ከእርሱ የተነሣ እንኖራለን—ሰቆ. 3፥22-24፣ 55-56፤ ራእ. 2፥4፣ 7፤ ዮሐ. 6፥57፣ 63፤ ኤር. 15፥16፤ ኤፌ. 6፥17-18፤ መዝ. 119፥15።

**II. እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ብቸኛው ኑሮ ክርስቶስ በምድር ላይ የኖረው ኑሮ መደገም ነው፤ ይህ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት በልምምዶቹ ክርስቶስን የሚለማመድ ሕይወት ነው—ዘሌ. 1፥9፤ ዮሐ. 8፥29፤ 2 ቆሮ. 5፥9፦**

ሀ. የሚቃጠለው መሥዋዕት ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር እርካታ የኖረውን ኑሮ በምሳሌ ያሳያል፤ የሚቃጠለው መሥዋዕት የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲህ ያለ ኑሮ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሕይወት በመሆኑም ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል—ዘሌ. 1፥3፤ ዘኍ. 28፥2-3፤ ዮሐ. 5፥30፤ 6፥38፤ 8፥29፤ ዕብ. 10፥5-10።

ለ. "የሚቃጠለው መሥዋዕት" ተብሎ የተተረጎመው ቃል የሚያርግን ነገር ያመላክታል፤ ይህ ማረግ ክርስቶስን ያመለክታል (ዘሌ. 1፥3፣ 10፣ 14)፤ ከምድር ወደ እግዚአብሔር ሊያርግ የሚችለው ብቸኛው ነገር በክርስቶስ የተኖረው ኑሮ ነው፣ ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የሆነ ሕይወት የኖረው ልዩና ብቸኛው ማንነት እርሱ ነውና (ዮሐ. 6፥38)።

ሐ. የሚቃጠለው መሥዋዕት "በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ" (ዘሌ. 1፥9) ነበር፤ "ጣፋጭ ሽታ" ተብለው የተተረጎሙት የዕብራይስጥ ቃላት በቀጥታ ሲተረጎሙ "የዕረፍት ወይም የእርካታ ጣዕም" ማለት ናቸው፤ የሚያረካ

ሽታ እርካታን፣ ሰላምን እና ዕረፍትን የሚያመጣ ጣዕም ነው፤ እንዲህ ያለው የሚያረካ ሽታ ለእግዚአብሔር ድሰታ ነው።

መ. በውስጣችን ያለው የክርስቶስ ሕይወት የሚቃጠለው መሥዋዕት እውነታ ነው—ይህ የመታዘዝ ሕይወት፣ የመገዛት ሕይወት እና በሕይወት ዛፍ መርህ መሠረት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ የመሆን ሕይወት ነው—ፊልጵ. 2፥8፤ ዮሐ. 5፥19፣ 30፤ ዕብ. 5፥8፤ 10፥7፦

1. ሰው ብቻውንና በኢ-ጥገኝነት ከእግዚአብሔር ተለይቶ እና ከእግዚአብሔር ውጭ [ነገሮችን] ማድረጉ ኃጢአት ነው፤ በነገር ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ መመሪያዎች መሠረት እንድናደርግ ይፈልጋል—መዝ. 40፥7-8፤ 1 ዮሐ. 3፥4።
2. "የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም" (ሉቃ. 18፥17)፤ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእርሱ ላይ ጥገኛ እንድንሆን ስለሚፈልግ ሁልጊዜ ልክ እንደ ትንሽ ሕፃን እንድንሆን ይፈልጋል፤ በራስ መተማመን የእግዚአብሔር-ጥገኛ የመሆን ጠላት ነው።

ሠ. ተገቢ በሆነ ጸሎት በኩል እንደሚቃጠለው መሥዋዕታችን በክርስቶስ ላይ እጆቻችንን በመጫን፣ ከእርሱ ጋር እንጋጠማለን፣ እርሱ እና እኛም አንድ እንሆናለን፤ ክርስቶስ በእኛ ሲኖር ሳለ፣ በምድር ላይ የኖረውን ኑሮ፣ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ኑሮ በእኛ ውስጥ ይደግመዋል—ዘሌ. 1፥4፤ 1 ቆሮ. 6፥17፤ ገላ. 2፥20፦

ረ. እንደዚህ ባለ ጥምረት፣ እንደዚህ ባለ አንድ መሆን ውስጥ ድካሞቻችን፣ እጥረቶቻችን እና ስሕተቶቻችን ሁሉ በእርሱ ይወሰዳሉ—2 ቆሮ. 5፥21፤ ገላ. 2፥20።

ሰ. ሌሎችን ለማንደድ የማያቋርጥ የሚቃጠል መሥዋዕት እንድንሆንና ለእግዚአብሔር መገለጥ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለመሆን ወደ አመድነት እንድንቀነስ ጌታ እንዲያነድደን መፍቀድ አለብን—መዝ. 20፥3፤ ዘሌ. 1፥16፤ 6፥8-13፤ 1 ቆሮ. 3፥12፤ ራእ. 3፥12፤ 21፥2፣ 10-11፣ 18-21፦

1. አመዱ ምንም ወደ መሆን የተቀነሰውን ክርስቶስ ያመለክታል፤ ወደ አመድነት ከተቀነሰው ክርስቶስ ጋር አንድ ስለሆንን፣ እኛም አመድ ወደ መሆን ተቀንሰናል፣ ማለትም፣ ምንም ወደ መሆን፣ ባዶ ወደ መሆን ተቀንሰናል—ማር. 9፥12፤ ኢሳ. 53፥3፤ 1 ቆሮ. 1፥28፤ 2 ቆሮ. 12፥11።
2. በሞቱ ከክርስቶስ ጋር ይበልጥ አንድ ስንሆን፣ የአመድ ክምር እንደሆንን ይበልጥ እንገነዘባለን፤ አመድ ስንሆን፣ ከዚያ በኋላ ተፈጥሮአዊ ሰው አንሆንም፤ በምትኩ የተሰቀልን፣ የተወገድን፣ የተቃጠልን ሰዎች እንሆናለን—ገላ. 2፥20።

ሸ. አመዱን ከመሠዊያው በምሥራቅ በኩል፣ በፀሐይ መውጫ በኩል ማስቀመጥ ትንሣኤን የሚያመለክት ነው—ዘሌ. 1፥16፤ ዮሐ. 11፥25፤ ፊልጵ. 3፥10-11፤ 2 ቆሮ. 1፥9፦

1. እንደ የሚቃጠለው መሥዋዕት ክርስቶስን [በተመለከተ]፣ አመዱ ፍጻሜ አይደለም—ጅማሬ ነው፤ የአመዱ ትርጉም ክርስቶስ ሞቷል ማለት ሲሆን፣ ምሥራቅ ግን ትንሣኤን ያመላክታል—ማር. 9፥31።
2. በክርስቶስ ይበልጥ ወደ አመድነት ስንቀነስ፣ ይበልጥ በምሥራቅ በኩል እንቀመጣለን፣ በምሥራቅ በኩል ደግሞ ፀሐይ እንደምትወጣ እና የትንሣኤን ፀሐይ መውጣት እንደምንለማመድ እርግጠኝነት ይኖረናል—ፊልጵ. 3፥10-11።

ቀ. በመጨረሻ፣ አመዱ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ይሆናል—ራእ. 3፥12፤ 21፥2፤ 10-11፦

1. የክርስቶስ ሞት ወደ ፍጻሜ ያመጣናል፣ አመድ ወደ መሆን ይቀንሰናል፣ በትንሣኤ አመዱ ለእግዚአብሔር ግንባታ የከበሩ የግንባታ ዕቃዎች ይሆናል—1 ቆሮ. 3፥9፣ 12።
2. ወደ አመድነት ስንቀነስ፣ ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገንባት የከበሩ የግንባታ ዕቃዎች እንሆን ዘንድ በሥስታንዱ አምላክ ወደ መለወጥ ውስጥ እንመጣለን—ሮሜ 12፥1-2፤ 2 ቆሮ. 3፥18፤ ራእ. 21፥18-21።

III. **የእግዚአብሔርን አዲስ ኪዳን አገልግሎት ሲያከናውን፣ ጌታ ኢየሱስ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት እውነታ፣ ምንም ነገር ከራሱ አላደረገም (ዮሐ. 5፥19)፣ የራሱን ሥራ አልሠራም (4፥34፤ 17፥4)፣ የራሱን ቃል አልተናገረም (14፥10፤ 24)፣ ሁሉንም ነገር በራሱ ፈቃድ አላደረገም (5፥30)፣ የራሱንም ክብር አልፈለገም (7፥18)፤ በእግዚአብሔርም ብቻ ረክቶ ስለነበር ፈጽሞ ቅር አልተሰኘም (ኢሳ. 42፥4፤ 50፥4-5፤ 53፥2፤ ተዛ. ዮሐ. 4፥13-14፤ 6፥15፤ ማር. 9፥7-8)፦**

ሀ. የጌታ ሕይወት ሥራው፣ እንቅስቃሴው እና አገልግሎቱ ነበር፤ ሥራው ኑሮው ነበር፣ እንቅስቃሴውም ማንነቱ ነበር፤ በእርሱ ዘንድ በሕይወቱ፣ በሥራው፣ በእንቅስቃሴው እና በአገልግሎቱ መካከል ምንም ልዩነት አልነበረም፤ ጌታ ኢየሱስ አገልግሎቱን ኖረ—ተዛ. ሉቃ. 22፥26-27፤ ዮሐ. 10፥10፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ 1 ዮሐ. 5፥16፤ 2 ቆሮ. 3፥6፤ ፊልጵ. 1፥25።

ለ. ጌታ ኢየሱስ የጸሎት ሰው ነበር፤ ለመጸለይ ብዙ ጊዜ ወደ ተራራ ወይም ብቻውን ወደሚሆንበት ስፍራ ይሄድ ነበር—ማቴ. 14፥23፤ ማር. 1፥35፤ ሉቃ. 5፥16፤ 6፥12፤ 9፥28።

ሐ. አምስት ሺህ ሰው ከተመገበበት ተአምር በኋላ፣ በግሉ ወደ አብ የሚጸልይበት ተጨማሪ ጊዜ ይኖረው ዘንድ ደቀ መዛሙርቱ ትተውት ይሄዱ ዘንድ ግድ አላቸው—ማቴ. 14፥22-23፦

1. ለመንግሥተ ሰማያት መመሥረት በምድር ላይ በሚያደርገው ነገር ሁሉ ከአብ ጋር አንድ ይሆንና አብ ከእርሱ ጋር ይሆን ዘንድ ሰማያዊው ንጉሥ እንደ የአብ የተወደደ ልጅ (3፥17) በሰው ስፍራ ላይ በመቆም (4፥4)፣ በሰማያት ወዳለው አባቱ በግል መጸለይ አስፈልጎት ነበር።
2. ይህንን ያደረገው በምድረ በዳ ሳይሆን ከአብ ጋር ለመገናኘት ብቻውን ይሆን ዘንድ ሰዎችን ሁሉ፣ ብሎም ደቀ መዛሙርቱን በመተው በተራራ ላይ ነበር።

መ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የነበረ የጸሎት ሰው ስለነበረ፣ ፈጽሞ ብቻውን አልበረም፣ ምክንያቱም አብ ከእርሱ ጋር ነበርና፤ በእያንዳንዱ አፍታ የአብን ፊት ይመለከት ነበር—ዮሐ. 5፥19፤ 16፥32፤ መዝ. 16፥7-8፤ ተዛ. 27፥8።

**IV. ፍቅር በሆነው በእግዚአብሔር በራሱ ውስጥ ስንኖር፣ "በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ <u>እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና</u>"** (1 ዮሐ. 4፥17)**፤ ክርስቶስ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት እውነታ ፍቅር የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕይወት በዚህ ዓለም ውስጥ ኖረ፣ ያንኑ የፍቅር ሕይወት በዚህ ዓለም ውስጥ እንድንኖር እና ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት እንድንሆን እርሱ አሁን ሕይወታችን ነው (3፥14፤ 5፥1፤ 2፥6)፦**

ሀ. በመንፈሳችን ውስጥ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ እንደ የፍቅር ሕግ የክርስቶስ ሕግ ነው (ሮሜ 8፥2፤ ገላ. 6፥2)፤ አንዳችን የሌላችንን ሸክሞች መሸከም እንችል ዘንድ የፍቅር ሕግ በሕይወት መንፈስ ሕግ ተጨባጭ መሆን አለበት፤ በትዕቢት ከተሞላን ግን፣ የሌሎችን ሸክሞች መሸከም ያቅተናል፣ ምክንያቱም ምንም ሳንሆን አንዳች የሆንን እየመሰለን ራሳችንን እናስታለንና (ቁ. 3)።

ለ. የፍቅር ሕግ በውስጣችን ሲቀሰቀስ፣ ኦቶማቲክ በሆነ መንገድ እና በቅጽበት የአባታችን የእግዚአብሔር አፍቃሪ እና ይቅር ባይ ልብ እና የአዳኛችን ክርስቶስ በእረኝነት የሚንከባከብ እና የሚፈልግ መንፈስ ያለን እረኞች እንሆናለን—ዮሐ. 21፥15-17፤ ሉቃ. 15፥3-7።

ሐ. የፍቅር ሕግ በውስጣችን ሲቀሰቀስ፣ በጌታ ያለን ድካም ደካሞችን የምንደግፍበት (ሐዋ. 20፥35) እና ደካሞችን የምንረዳበት (1 ተሰ. 5፥14) የፍቅር ድካም ይሆናል (1 ቆሮ. 15፥58፤ 1 ተሰ. 1፥3)፤ *ደካሞች* የሚያመለክተው በመንፈሳቸው ወይም በነፍሳቸው ወይም በአካላቸው ደካማ የሆኑትን፣ ወይም በእምነት ደካማ የሆኑትን ነው (ሮሜ 14፥1፤ 15፥1)።

መ. ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ጴጥሮስን በእረኝነት ተንከባከበው፣ ጠቦቶቹን እንዲመግብ እና በጎቹን እንዲጠብቅም ተልእኮ ሰጠው፤ ይህ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መፈጸም አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ የክርስቶስ አካል መገንባትን የሚያመጣውን የእግዚአብሔርን መንጋ፣ ቤተ ክርስቲያንን ለመንከባከብ ሐዋርያዊውን አገልግሎት ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር ማካተት ነው—ዮሐ. 21፥15-17።

*© 2026 Living Stream Ministry*

መልእክት አራት

**እንደ መለኮታዊው ዝርያ ክልል**
**በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በመኖር**
**የአምላክ-ሰው ሕይወትን መኖር**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ማር. 1፥15፤ ዮሐ. 3፥3፣ 5-6፤ 1፥12-13፤
2 ጴጥ. 1፥4፤ 1 ዮሐ. 3፥1

I. **ከእግዚአብሔር ስለተወለድን፣ የእግዚአብሔር ዝርያዎች ነን፤ ማለትም፣ በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ነን—ዮሐ. 3፥3፣ 5-8።**

II. **አምላክ-ሰዎች በአምላክ ዝርያ ውስጥ የመሳተፍ መለኮታዊ መብት አላቸው—ቁ. 3፣ 5-6፤ 18፥36።**

III. **በክርስቶስ እንደሚያምኑ አማኞች፣ የአምላክ-ሰው ኑሮን እየኖርን ነው—ማር. 1፥15፤ ዮሐ. 14፥17፣ 20፤ ሮሜ 8፥9፣ 10፤ ገላ. 5፥25፦**

ሀ. በክርስቶስ እግዚአብሔር ወደ ሰው ውስጥ ተቀናብሯል፣ ሰው ወደ እግዚአብሔር ውስጥ ተቀናብሯል፣ እግዚአብሔርና ሰውም አምላክ-ሰው ተብሎ የሚጠራ አንድ አካል ለመሆን ተዋሕደዋል—ማቴ. 1፥21፣ 23፤ ሉቃ. 1፥35፤ ቲቶ 2፥13፤ 1 ጢሞ. 2፥5።

ለ. አምላክ-ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ልጆች፣ የመጀመሪያው አምላክ-ሰው የክርስቶስ መባዛት እና መቀጠል ናቸው—ዮሐ. 12፥24፤ ዕብ. 2፥10፤ ሮሜ 8፥29።

ሐ. አምላክ-ሰው ማለት ከእግዚአብሔር የተወለደና የእግዚአብሔርን ሕይወትና ባሕርይ የሚካፈል፣ በሕይወቱና በባሕርይው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆነ በዚህም እርሱን የሚገልጥ ነው—ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥15፤ 2 ጴጥ. 1፥4፤ 1 ቆሮ. 6፥17።

መ. አምላክ-ሰው እግዚአብሔር አንደ ሕይወቱ፣ ባሕርይው እና ሁሉ ነገሩ ያለው በእግዚአብሔር የተቀናበረ ነው፤ አምላክ-ሰው፣ ሰው ሆኖም አምላክ ነው፣ አምላክ ሆኖም ሰው ነው—ኤፌ. 3፥16-17።

ሠ. የክርስቶስ የስብዕና ኑሮ በመለኮታዊ ባሕርያት በተሞሉ፣ በተዋሃዱና ፈጽመው በተሞሉ በሰው ሰናይ ባሕርያት ውስጥ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ለመግለጥ ሰው እግዚአብሔርን መኖሩ ነበር—ሉቃ. 1፥26-35፤ 7፥11-17፤ 10፥25-37፤ 19፥1-10።

ረ. የመጀመሪያው አምላክ-ሰው ርቢ እና ብዜት እንደመሆናችን፣ እርሱ የኖረውን ዓይነት ኑሮ መኖር አለብን፦

1. የጌታ የአምላክ-ሰው ኑሮ ለእኛ የአምላክ-ሰው ኑሮ ሞዴልን አስቀምጦልናል—እግዚአብሔር በስብዕና ይገለጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመኖር መሰቀል—ገላ. 2፥20።
2. ጌታ ኢየሱስ መንፈሳዊ፣ ቅዱስና አሸናፊ ለመሆን የመሞከርን ኑሮ አልኖረም፤ እርሱ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ መሠረትና ለእግዚአብሔር የአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ የሆነ ኑሮ ኖረ።
3. በአራቱ ወንጌላት ኢየሱስ የአምላክ-ሰውን ኑሮ ሲኖር እናያለን፣ በሐዋርያት ሥራ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም እንዲህ ያለውን ኑሮ ሲኖሩ እናያለን።
4. ክርስቶስ መከራ የመቀበል ኑሮ፣ የመከራ ሕይወት ኖረ፤ አሁን እኛ ያንኑ ዓይነት ሕይወት የምንኖር የእርሱ አጋሮች ነን፤ ስለ ክርስቶስ መከራ ስንቀበል፣ መከራዎቻችን በእግዚአብሔር ዘንድ የክርስቶስ መከራዎች ተደርገው ይቆጠራሉ—ዕብ. 3፥14።
5. ራሳችንን መካድ፣ የክርስቶስን ሞት መምሰል እና በመንፈሱ የተትረፈረፈ አቅርቦት እርሱን ማጉላት አለብን—ማቴ. 16፥24፤ ፊልጵ. 3፥10፤ 1፥19-21።
6. የአምላክ-ሰውን ኑሮ የኖረው አሁን በእኛ ውስጥና በእኛ በኩል የሚኖረው መንፈስ ነው፤ ራስን ማዳበርንና ተፈጥሯዊ ሰዋችንን መገንባትን መተው አለብን፣ እርሱን እንድንኖርና እርሱን በግልና አካሉ በሆነችው በቤተ ክርስቲያን በጋራ እንገልጠው ዘንድም ከእርሱ ማንነት በቀር ሌላ ምንም ነገር እንዲሞላንና እንዲይዘን መፍቀድ የለብንም—ኤፌ. 3፥16-19፤ 1፥22-23።

IV. **በክርስቶስ እንደሚያምኑ አማኞች፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እየኖርን ነው—ሮሜ 14፥17፦**

ሀ. የእግዚአብሔር መንግሥት እግዚአብሔር ራሱ ነው—ማር. 1፥15፤ ማቴ. 6፥33።

ለ. የእግዚአብሔር መንግሥት እግዚአብሔር በክርስቶስ፣ ከተግባሮቹ ሁሉ ጋር የመለኮታዊው ሕይወት ጥቅል ድምር መሆኑ ነው—ዮሐ. 11፥25፤ 10፥10፤ 14፥6።

ሐ. የእግዚአብሔር መንግሥት [መለኮታዊው ሕይወት] ዓላማውን ይፈጽም ዘንድ ይህ ሕይወት እንዲንቀሳቀስ፣ እንዲሠራ፣ እንዲገዛና እንዲያስተዳድር የመለኮታዊው ሕይወት ክልል ነው።

መ. የእግዚአብሔር መንግሥት እግዚአብሔር ይገዛ ዘንድ እንደ የሕይወት ክልል በእርሱ ሕይወት የተቀናበረ ሕይወታዊ አካል ነው፣ በዚህም በሕይወቱ ይነግሣል በመለኮታዊው ሕይወት እንደ መለኮታዊው ሥላሴ ራሱንም ይገልጣል—15፥1-8፣ 16፣ 26።

ሠ. የእግዚአብሔር መንግሥት የመለኮታዊው ግዛት ክልል ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ነገሮች ሁሉ ያሉበት የመለኮታዊው ዝርያ ክልልም ጭምር ነው—3፥3፣ 5-6፤ 18፥36፡-

1. በዮሐንስ 3 የእግዚአብሔር መንግሥት ከእግዚአብሔር አገዛዝ ይልቅ የእግዚአብሔርን ዝርያ ያመላክታል።
2. እግዚአብሔር ወደ ሰው ዝርያ ውስጥ ለመግባት ሰው ሆነ፣ ሰውም ወደ መለኮታዊ ዝርያ ክልል ለመግባት በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነትን ሳይጨምር እግዚአብሔርን ይሆናል—1፥1፣ 12-14፤ ሮሜ 8፥3፤ 1፥3-4።
3. ወደ መለኮታዊ ዝርያ ክልል ለመግባት፣ መለኮታዊ ሕይወትና መለኮታዊ ባሕርይ ይኖረን ዘንድ ከእግዚአብሔር መወለድ ያስፈልገናል—ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥3፣ 5-6፣ 15፤ 2 ጴጥ. 1፥4፡-
   - ሀ. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው እንደ ሰው ወገን ሳይሆን የእግዚአብሔር ወገን፣ የእግዚአብሔር ዝርያ ይሆን ዘንድ በመልኩና በምሳሌው ነው—ዘፍ. 1፥26።
   - ለ. በሕይወቱና በባሕርይው ተመላኪነቱን ሳይጨምር ልጆቹ ለመሆን በዳግም ውልደት ከእግዚአብሔር የተወለዱት አማኞች ከአዳም ይልቅ የእግዚአብሔር ወገን ናቸው—ዮሐ. 1፥12-13፡-
     - (1) አዳም ያለ የመለኮታዊ ሕይወት ውስጣዊ እውነታ ውጫዊ መልክ ብቻ ነበረው።
     - (2) በክርስቶስ የምናምንና የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን እኛ የመለኮታዊው ሕይወት እውነታ አለን፣ በመላው ማንነታችንም ወደ ጌታ መልክ እየተለወጥንና የጌታን መልክ እየመሰልን ነው—2 ቆሮ. 3፥18፤ ሮሜ 12፥2፤ 8፥29።
     - (3) ሁለተኛ ውልደታችን፣ ዳግም መወለዳችን፣ የእግዚአብሔር ዝርያ ለመሆን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንድንገባ አድርጎናል—ዮሐ. 3፥3፣ 5-6።
     - (4) የእግዚአብሔር ወገን ለመሆን ዳግም ተወልደናል፤ እንደ የእግዚአብሔር ልጆች፣ የእግዚአብሔር ወገን፣ የእግዚአብሔር ዝርያ ነን—ሮሜ 8፥19፤ ዕብ. 2፥10።
     - (5) የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በመለኮታዊው ዝርያ መለኮታዊ ክልል ውስጥ ናቸው—ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥3፣ 5።
     - (6) አማኞች በመለኮታዊ ዝርያ ውስጥ፣ ማለትም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉ አምላክ-ሰዎች ናቸው—1 ዮሐ. 3፥1፤ ዮሐ. 3፥5።

ረ. እንደ መለኮታዊው ሕይወት ክልል በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የምንኖረው በሕይወት ስሜት ነው—ሮሜ 8፥6።

ሰ. በቤተ ክርስቲያን፣ ዛሬ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እየኖርን ነው፤ ሮሜ 14፥17 የዛሬው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት መንግሥቱ እንደሆነ ጠንካራ ማረጋገጫ ነው።

ሸ. አዲሱ ፍጥረት—እንደ የእግዚአብሔር መንግሥት ንጥረ-ነገር ክርስቶስ ራሱ—የሆነውን ክፍላችንን ስናንቀሳቅስ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እየኖርን ነው።

ቀ. ወደ መንግሥተ ሰማያት መገለጥ መግባት ይችሉ ዘንድ ድል ነሺዎቹ የክርስቶስንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ይወርሳሉ—2 ጢሞ. 4፥18።

## V. በዮሐንስ ወንጌል በመለኮታዊው ዝርያ ክልል ውስጥ የአማኞችን ኑሮ ብዙ ገጽታዎች እናያለን—1፥16፤ 15፥4፣ 9፣ 11፤ 4፥23-24፤ 14፥2፣ 20፣ 23፤ 17፥22-24፡-

ሀ. "እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና"—1፥16።

ለ. "እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል"—4፥14።

ሐ. “የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል”—6፥57
መ. “የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል”—12፥26።
ሠ. “በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ”—14፥2።
ረ. “እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ”—ቁ. 20።
ሰ. “የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን”—ቁ. 23።
ሸ. “በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ”—15፥4።
ቀ. “በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል”—ቁ. 7።
በ. “አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ”—ቁ. 9።
ተ. “ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ”—ቁ. 11።
ቸ. “በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ”፤ “ሰላሜን እሰጣችኋለሁ”—16፥33; 14፥27።
ኀ. “ቅዱስ አባት ሆይ፣ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው”—17፥11።
ነ. “እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ”—ቁ. 22።
ኘ. “እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፣ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ”—ቁ. 23።
አ. “አባት ሆይ...ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ”—ቁ. 24።

*© 2026 Living Stream Ministry*

መልእክት አምስት

## ለክርስቶስ አካል ግንባታ እና ለአዲስ መነቃቃት
## የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንደ የእርሱ መንጋ በእረኝነት ለመንከባከብ
## ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር በመተባበር የሆነው ሐዋርያዊ አገልግሎት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- ዮሐ. 10፥11፥ 16፤ 21፥15-17፤
1 ጴጥ. 2፥25፤ 5፥4፤ ዕብ. 13፥20፤ ራእ. 1፥13፤ 2፥1፣ 7

**I. መዝሙር 22 እስከ 24፣ ከስቅለቱ ጀምሮ በእረኝነት እንክብካቤው በኩል እስከሚመጣው ዘመን ንግሥናው ድረስ ክርስቶስን የሚገልጡ የመዝሙሮች ስብስብ ናቸው፡-**

ሀ. በትንሣኤው እና በዕርገቱ እንዳለ እረኛ ክርስቶስን የሚመለከተው መዝሙር 23፣ በመዝሙር 22 ባለው በክርስቶስ የሚቤዥ ሞት እና ቤተ ክርስቲያንን በሚያፈራ ትንሣኤው እና በመዝሙር 24 አካሉ በሆነችው በቤተ ክርስቲያን በኩል መላውን ምድር መልሶ የራሱ እንደሚያደርገው ንጉሥ ተመልሶ በሚመጣው ክርስቶስ መካከል ያለ ድልድይ ነው።

ለ. በሰማያዊው አገልግሎቱ ክርስቶስ ሰዎችን በእረኝነት እየተንከባከበ ነው፤ እኛም ሰዎችን በእረኝነት በመንከባከብ ከእርሱ ጋር መተባበር አለብን፤ ይህን ኅብረት ከተቀበልን፣ ጌታን መልሶ ለማምጣት ታላቅ መነቃቃት በምድር ላይ ይሆናል።

**II. ዮሐንስ 21 ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር በመተባበር የሆነውን ሐዋሪያዊ አገልግሎት ይገልጣል፤ ስለዚህ የዮሐንስ ወንጌል ፍጻሜና መጠናቀቅ ነው፡-**

ሀ. የዮሐንስ ወንጌል ሃያ አንድ ምዕራፎች አሉት፣ በእርግጥ ግን ይህ መጽሐፍ የሚደመደመው በምዕራፍ 20 ነው።

ለ. መላዉ መጽሐፍ፣ ክርስቶስ በሥጋ ያለ ሰው ለመሆን እንደ የእግዚአብሔር ቃል ሥጋ በመልበሱ በመጀመር (1፥14)፣ እንደ ኋለኛው አዳም ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ ለመሆን በትንሣኤው በመደምደም (20፥22) የክርስቶስን ምድራዊ አገልግሎት ይሸፍናል፤ በመሆኑም፣ ምዕራፍ 21 አባሪ መሆን አለበት።

ሐ. ይህን ማለት ትክክል ቢሆንም፣ ዮሐንስ 21 የዮሐንስ ወንጌል ፍጻሜና ማጠናቀቂያ እንደሆነ መናገር ይበልጥ ውስጠ-መሠረታዊ ነው፤ የክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት እና በምድር ላይ ያለው የሐዋሪያት አገልግሎት የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ለማከናወን በአንድ ላይ እንደሚተባበሩ በማሳየት መላውን የዮሐንስ ወንጌል ያጠናቅቃል።

**III. በዮሐንስ 10፡10-11 እና 16 ጌታ፣ በጎቹ ሕይወት እንዲበዛላቸው የመጣው መልካም እረኛ መሆኑን እና ሌሎች በጎች (አሕዛብ) እንዳሉት፣ ከእነርሱም (ከአይሁድ አማኞች) ጋር ተጋጥመው በአንድ እረኛ ሥር ያሉ አንድ መንጋ (አንድ ቤተ ክርስቲያን) እንዲሆኑ ሊመራቸው እንደሚገባ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጦላቸዋል፡-**

ሀ. የጌታ እረኝነት በመጀመሪያ፣ በምድራዊ አገልግሎቱ ነበር—ማቴ. 9፥36፤ ተዛ. 10፥1-6።

ለ. የጌታ እረኝነት፣ አካሉ የምትሆነውን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመንከባከብ በሰማያዊ አገልግሎቱ ሁለተኛ ነው (1 ጴጥ. 5፥4)።

**IV. ጌታ ጠቦቶቹን እንዲመግብና በጎቹን እንዲያሰማራ ጴጥሮስን አዘዘው፡-**

ሀ. ጌታ ከትንሣኤው በኋላ እና ከዕርገቱ በፊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በቆየ ጊዜ፣ ከመገለጦቹ በአንዱ፣ እርሱ በማይኖር ጊዜ፣ በሰማያት ሳለ ጠቦቶቹን እንዲመግብና በጎቹን እንዲያሰማራ ለጴጥሮስ ተልእኮ ሰጠው—ዮሐ. 21፡15-17።

ለ. ይህ የእግዚአብሔርን መንጋ፣ እርሷም የክርስቶስ አካል የምትሆነውን ቤተ ክርስቲያንን ለመንከባከብ ሐዋሪያዊውን አገልግሎት ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር ማካተት ነው።

ሐ. ኋላም፣ በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ጴጥሮስ "እኛ ግን በጸሎት እና በቃሉ አገልግሎት እንተጋለን" ብሏል (6፥4 አ.መ.ት.)፤ ይህ ከክርስቶስ የምልጃ (ዕብ. 7፥25) እና እግዚአብሔርን ወደ ሕዝቦቹ ውስጥ የማገልገል (8፥2) ሰማያዊ አገልግሎት ጋር መተባበር ነው።

መ. ጴጥሮስ በዚህ የጌታ ተልዕኮ እጅግ ስለተመሰጠ በመጀመሪያው መጽሐፉ አማኞች እንደ በጎች ሲቅበዘበዙ እንደነበረ፣ አሁን ግን ወደ ነፍሳቸው እረኛና ጠባቂ እንደተመለሱ ይነግራቸዋል—1 ጴጥ. 2፥25፡-

1. ክርስቶስ ሕይወታችን እና ሁሉ ነገራችን ይሆን ዘንድ በውስጣችን ይኖራል፤ በተጨማሪም የውስጥ ማንነታችን ያለበትን ሁኔታ እና ተጽዕኖ የሚያደርግበትን ውጫዊ ሁኔታ እየቃኘ፣ እየተመለከተ ነው።

2. ለውስጥ ማንነታችን ደኅንነት ግድ በመሰኘት እና የነፍሳችንን፣ የእውነተኛ ማንነታችንን ሁኔታ በመቃኘት በእረኝነቱ ይንከባከበናል—ተዛ. ዕብ. 13፥17።

ሠ. የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ፣ ታማኞቹ ሽማግሌዎች የማያልፈውን የክብር አክሊል ይቀበሉ ዘንድ በእነርሱ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት እንዲንከባከቡ ጴጥሮስ ሽማግሌዎችን ይመክራል—1 ጴጥ. 5፥1-4።

ረ. የጴጥሮስ ቃል፣ የክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት በዋናነት፣ ውጤቱ አካሉ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ መንጋ በእረኝነት መንከባከብ እንደሆነ ያመላክታል።

**V. የሚከተሉት የሐዋሪያው ጳውሎስ ቃላት የእግዚአብሔርን መንጋ ለመንከባከብ ሐዋሪያዊው አገልግሎት ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር መካተቱንም ያሳያሉ፡-**

ሀ. በሐዋሪያት ሥራ 20፡28 ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉ ሽማግሌዎች፣ “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ” ብሏቸዋል።

ለ. ጳውሎስ፣ “ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ እኔ አውቃለሁ” ብሏል (ቁ. 29)፤ ሐዋሪያው ለራሱ ሕይወት ግድ አልተሰኘም (ቁ. 24)፤ ነገር ግን ለእርሱና ለእግዚአብሔር ውድ ሃብት ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን ወደፊት ለሚገጥማት ነገር እጅግ ግድ ተሰኝቶ ነበር።

ሐ. በዕብራውያን 13፥20 ጳውሎስ፣ “በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው ...አምላክ” ይላል፡-

1. ዘላለማዊው ኪዳን አንድን መንጋ፣ ይህም አካሉን የምታፈራውን እና በአዲሰቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ቤተ ክርስቲያንን ለማግኘት የሆነው የአዲስ ኪዳን ኪዳን ነው፤ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኪዳን በእረኝነት አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ማጠናቀቅ ነው።
2. በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኪዳን መሠረት አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ ታላቁ እረኛ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ጌታችንን ከሞት አስነሣው።

**VI. ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር የተካተተው የሐዋሪያዊው አገልግሎት ዋና ዓላማና ግብ፣ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መፈጸም በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀውን የክርስቶስን አካል መገንባት ናቸው—ተዛ. ኤፌ. 3፥2፣ 8-9፤ 1 ጴጥ. 5፥10።**

**VII. ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ዋና ዓላማ እና ከፍተኛ-የመጨረሻ መጠናቀቅ የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት የመንከባከብ ጉዳይ በመኃልየ መኃልየ እንኳን ተጠቅሷል፡-**

ሀ. “ነፍሴ የወደደችህ አንተ ንገረኝ፤ [ለእርካታ መንጋህን] ወዴት ታሰማራለህ? በቀትርስ ጊዜ [ለእረፍት] ወዴት ትመስጋለህ?”—1፥7።

ለ. “የመንጎችን ፍለጋ ተከትለሽ ውጪ፥ የፍየል ግልገሎችሽንም በእረኞች ድንኳኖች አጠገብ አሰማሪ”—ቁ. 8።

ሐ. “ውዴ የእኔ ነው፣ እኔም የእርሱ ነኝ፤ በሱፍ አበባዎች [በነጠላ ልብ በእግዚአብሔር የመታመንን ሕይወት በሚኖሩ በክርስቶስ ፈላጊዎች] መካከልም መንጋውን ያሰማራል—2፥16።

መ. “እኔ የውዴ ነኝ ውዴም የእኔ ነው፤ በሱፉ አበባ መካከል መንጋውን ያሰማራል”—6፥3።

**VIII. አማኞችን በእረኝነት መንከባከብ በሕይወት ለማደጋቸው እጅግ ወሳኝ ነው፤ ወንጌልን ለመስበክ እና ቤተ ክርስቲያንን ለማነቃቃት በእረኝነት የመንከባከብን መንገድ መውሰድ አለብን፡-**

ሀ. “ጌታ ሆይ መነቃቃት እፈልጋለው፤ ከዛሬ ጀምሬ እረኛ መሆን እፈልጋለው፤ ሰዎችን ለመመገብ፣ ሰዎችን በእረኝነት ለመንከባከብ እና እንደ መንጋ ለማሰማራት መሄድ እፈልጋለው” ብለን መጸለይ አለብን።

ለ. በዮሐንስ 10 እና 21 ጌታ እረኝነትን በተመለከተ ሦስት ቃላትን ተጠቅሟል፡- *መግብ፣ ጠብቅ፣ እና አሰማራ* (10፥16፤ 21፥15-16)፤ *መንጋ* የሚለውን ቃል እንደ ግስም መጠቀም እንችላለን።

ሐ. ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ላይ መገጣጠም ይችሉ ዘንድ እንደ መንጋ እንዴት መሰብሰብ እንዳለባቸው መማር አለባቸው፤ ይህንን በተግባር ለመለማመድ ሽማግሌዎች እና አብሮ ሠራተኞች ቅድሚያውን መውሰድ አለባቸው።

IX. **የወርቃማው መቅረዝ በሕይወት መጠበቅ፣ በሕይወታዊ እረኝነቱ በኩል ድል ነሺዎችን ለማፍራት አብያተ ክርስቲያናትን በስብዕናው ለማስደሰት እና አብያተ ክርስቲያናትን በመለኮትነቱ ለመመገብ የሆነው የክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ነው—ራእ. 1፥13፤ 2፥7፤ ዮሐ. 10፥11፣ 14፤ 1 ጴጥ. 2፥25፤ 5፥4፤ ዕብ. 13፥20፦**

ሀ. የሰው ልጅ በስብዕናው ነው፤ የወርቅ መታጠቂያው መለኮትነቱን ያመለክታል፤ ደረት ደግሞ የፍቅር ምልክት ነው፦

1. ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናትን ለማፍራት ወገቡን ታጥቆ፤ ለመለኮታዊው ሥራ ጠንክሮ ነበር (ዘጸ. 28፡4፤ ዳን. 10፡5)፤ አሁን ግን ደረቱን ታጥቆ፣ በፍቅሩ ያፈራቸውን አብያተ ክርስቲያናትን እየተንከባከበ ነው(ራእ. 1፥13)።
2. የወርቁ መታጠቂያ እንደ መለኮታዊ ጉልበቱ የክርስቶስን መለኮትነት ያመላክታል፤ ደረት፣ ይህ ወርቃማ ጉልበት የሚንቀሳቀሰውና የሚነሣሣው አብያተ ክርስቲያናትን ለመመገብ በፍቅሩ አማካኝነት እና ከፍቅሩ ጋር መሆኑን ያመለክታል።

ለ. ክርስቶስ እንደ ሰው ልጅ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስደሰት በስብዕናው ይንከባከባቸዋል—ቁ. 13፦

1. ተገቢ እንዲሆኑ ለማድረግ የመቅረዞቹን መብራት ያስተካክላል፤ ደስተኞች፣ ደስ የምናሰኝ እና ምቾት ያለን እንሆን ዘንድ ያስደስተናል—ዘጸ. 30፥7፤ ተዛ. መዝ. 42፥5፣ 11፦
   - ሀ. የጌታ መገኘት ዕረፍትን፣ ምቾትን፣ ፈውስን፣ መንጻትንና መበረታታትን ለእኛ በመስጠት ማንነታችንን ለማስደሰት ሩኅሩኅና የሞቀ ድባብን ያመጣል።
   - ለ. የሕይወትን የሚመግብ አቅርቦት ለመቀበል በቤተ ክርስቲያን የጌታን መገኘት አስደሳች ድባብ መደሰት እንችላለን—ኤፌ. 5፥29፤ ተዛ. 1 ጢሞ. 4፥6፤ ኤፌ. 4፥11።
2. ማብራታችንን የሚያስተጓጉሉ አሉታዊ ነገሮችን ሁሉ በመቁረጥ የመቅረዞቹን መብራቶች ክሮች ይቀረቅማል—ዘጸ. 25፥38፦
   - ሀ. የክሩ የተቃጠለው ክፍል፣ የሚጤሰው ክፍል፣ በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት ያልሆኑትን እና መቆረጥ የሚያስፈልጋቸውን እንደ ሥጋችን፣ ተፈጥሮአዊ ሰዋችን፣ እኔነታችንና አሮጌ ፍጥረታችን ያሉ ነገሮችን ያመለክታል።
   - ለ. አብያተ ክርስቲያናት በውስጠ-ነገር፣ በገጽታ እና በመገለጥ አንድ ዓይነት ይሆኑ ዘንድ በመካከላቸው ያሉትን ልዩነቶች (ስህተቶች፣ እጥረቶች፣ ውድቀቶችና እንከኖች) ሁሉ ይቀረቅማል—ተዛ. 1 ቆሮ. 1፥10፤ 2 ቆሮ. 12፥18፤ ፊልጵ. 2፥2።

ሐ. ክርስቶስ፣ አብያተ ክርስቲያናትን ለመመገብ በደረቱ ላይ ባለው የወርቅ መታጠቂያ ከተመላከተው ከመለኮታዊ ፍቅሩ ጋር በመለኮትነቱ አብያተ ክርስቲያናትን ይንከባከባቸዋል—ራእ. 1፥13፦

1. ዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ለመፈጸም ድል ነሺዎቹ እንሆን ዘንድ በመለኮታዊው ሕይወት እንድናድግ እና እንድንበስል ሦስት ደረጃዎች ባለው ሙሉ አገልገሎቱ ሁሉን እንዳካተተው ክርስቶስ ራሱን ይመግበናል።
2. እንደሚመላለሰው ክርስቶስ፣ የእያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ያውቃል፤ እንደ ሚናገረው መንፈስ፣ መቅረዞቹን በመቀርቀም በትኩስ ዘይት፣ በመንፈስ አቅርቦት ይሞላል—2፥1፣ 7፤ ተዛ. ዘጸ. 27፥20-21፤ ዘካ. 4፥6፣ 11-14።
3. በእንቅስቃሴው ለመሳተፍ እና እንክብካቤውን ለመደሰት፣ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መሆን አለብን።

X. **በክርስቶስ ድንቅ እረኝነት በኩል፣ እርሱን እንደ በረከታችን ዛሬም፣ ለዘላለምም እንደሰተዋለን—ኢሳ. 49፥10፤ ራእ. 7፥9-17፤ ዮሐ. 6፥35፤ 4፥13-14፤ መዝ. 36፥7-9፤ 91፥1፤ ኢሳ. 12፥1-6፤ ራእ. 22፥1።**

*© 2026 Living Stream Ministry*

መልእክት ስድስት

## በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዮሐ. 21፥15-17፤ ሐዋ. 20፥28፤ 1 ጴጥ. 5፥2፣ 4፤ ኤፌ. 4፥16

**I. ዛሬ በጌታ ምለሳ የእረኝነት አንገብጋቢ አስፈላጊነት አለ።**

**II. በእረኝነት መንከባከብ ማለት ለመንጋው ሁሉን-ያካተተ ለስላሳ እንክብካቤ መስጠት ነው—ዮሐ. 21፥15-17፤ ሐዋ. 20፥28፦**

ሀ. እረኝነት በጎቹ ለሚያስፈጋቸው ነገሮች ሁሉ ግድ መሰኘትን ያመለክታል።

ለ. ሁሉም በጎች በቂ አቅርቦት እና ጥሩ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል።

**III. ክርስቶስ መልካሙ እረኛ፣ ታላቁ እረኛ፣ የእረኞች አለቃ እና የነፍሳችን እረኛ ነው—ዮሐ. 10፥9-17፤ ዕብ. 13፥20-21፤ 1 ጴጥ. 5፥4፤ 2፥25፦**

ሀ. እንደ መልካሙ እረኛ፣ ጌታ ኢየሱስ ሕይወት እንዲሆንልንና እንዲበዛልን መጣ—ዮሐ. 10፥10-11፦

1. በጎቹ ዞዌ ሕይወቱን፣ መለኮታዊ ሕይወቱን ይካፈሉ ዘንድ ለእነርሱ ቤዛነትን ለመፈጸም የነፍስ ሕይወቱን፣ የሰብዕና ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ—ቁ. 11፣ 15፣ 17።
2. የራሱን በጎች ከበረት አውጥቶ፣ እርሱን በነጻነት ወደሚበሉበት እና በእርሱ ወደሚመገቡበት፣ መሰማሪያ፣ የመመገቢያ ስፍራ ወደ ሆነው ወደ ራሱ ውስጥ ይመራቸዋል—ቁ. 9።
3. ጌታ በእረኝነቱ አይሁድ እና አሕዛብ አማኞችን አንድ መንጋ (ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ አካል) አድርጎ ሠርቷቸዋል—ቁ. 16።

ለ. "በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን" እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው—ዕብ. 13፥20፦

1. ዘላለማዊው ኪዳን በእረኝነት አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ማጠናቀቅ ነው።
2. ዘላለማዊው ኪዳን፣ መንጋን፣ የክርስቶስን አካል የምታመጣውንና በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ቤተ ክርስቲያንን ለማግኘት የሆነው አዲሱ ኪዳን ኪዳን ነው።

ሐ. እንደ የእረኞች አለቃ፣ ክርስቶስ በአብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች በኩል መንጋውን በእረኝነት ይንከባከባል—1 ጴጥ. 5፥4፦

1. ያለ ሽማግሌዎች እረኝነት ቤተ ክርስቲያን ልትገነባ አትችልም።
2. የሽማግሌዎች እረኝነት የክርስቶስ በእነርሱ በኩል በእረኝነት መንከባከቡ መሆን አለበት።

መ. እንደ የነፍሳችን እረኛ፣ እስትንፋሳዊው ክርስቶስ ለውስጥ ማንነታችን ሁኔታ ግድ በመሰኘት ውስጣዊ ሁኔታችንን ይቆጣጠራል—2፥25፦

1. ለነፍሳችን ደኅንነት ግድ በመሰኘት እና የውስጥ ማንነታችንን ሁኔታ በመከታተል በእረኝነት ይንከባከበናል።
2. ነፍሳችን እጅግ ውስብስብ ስለሆነች፣ አእምሮአችንን፣ ስሜታችንን እና ፈቃዳችንን እና ችግሮቻችንን፣ የሚያስፈልጉንን ነገሮች እና ቁስሎቻችንን ለመንከባከብ፣ ነፍሳችንን በእረኝነቱ ይንከባከብ ዘንድ ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ የሆነው በመንፈሳችን ውስጥ ያለው ክርስቶስ ያስፈልገናል።

**IV. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ለመንከባከብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን፣ በእግዚአብሔር መቀናበር፣ እግዚአብሔርን መኖር፣ እግዚአብሔርን መግለጥ፣ እግዚአብሔርን መወከል እና እግዚአብሔርን ለሌሎች ማገልገል ያስፈልገናል፦**

ሀ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆናችንን እና በእግዚአብሔር መቀናበራችንን ይጠይቃል—ዮሐ. 14፥20፤ 1 ቆሮ. 6፥17፤ ኤፌ. 3፥17፤ ቆላ. 3፥10-11።

ለ. እግዚአብሔርን የሚኖሩ ብቻ በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ሊንከባከቡ ይችላሉ—ፊልጵ. 1፥21።

ሐ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ እርሱን እንገልጠው ዘንድ ራሱን እንደ ሕይወታችን ወደ ውስጣችን መሥራት ነው—ዘፍ. 1፥26፤ ኤፌ. 1፥11፤ 3፥11፤ 2 ጢሞ. 1፥9።

መ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት እንደሚንከባከቡ ሰዎች፣ እግዚአብሔርን መወከል እና እንደ እግዚአብሔር ወኪል ማገልገል ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 1፥3-4፣ 12፣ 15-16፤ 2፥10፤ 10፥11፤ 11፥2።

ሠ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ እግዚአብሔርን ለሌሎች ማገልገል ነው፦

1. እግዚአብሔርን ለሌሎች ማገልገል የምንችልበት መጠን፣ ሕይወት [በእኛ] ሞልቶ ይፈስ ዘንድ በእግዚአብሔር በመሰበራችን ላይ ይመረኮዛል—4፥10-12፤ 16፤ ዕብ. 4፥12።
2. አንዳችን ለሌላችን እግዚአብሔርን ማገልገል ከፈለግን፣ ወደ ማንነታችን ውስጥ የተሠራውን በሂደት ያለፈውን አምላክ በማገልገል የጸጋን፣ የእውነትን፣ የመንፈስን እና የሕይወትን ቃላት መናገር ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፥16-17፤ 4፥25፣ 29፤ ዮሐ. 6፥63።

**V. ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን መንጋ በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት እንዲንከባከቡ ሽማግሌዎችን አዘዛቸው—1 ጴጥ. 5፥2፦**

ሀ. *በእግዚአብሔር መሠረት* ማለት እግዚአብሔርን መኖር አለብን ማለት ነው።

ለ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ስንሆን፣ እግዚአብሔርን እንሆናለን፣ ሌሎችን በእረኝነት በመንከባከባችንም ውስጥ እግዚአብሔር ነን።

ሐ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ በምርጫችን፣ በፍላጎታችን፣ በዓላማችን እና በግል ጸባያችን መሠረት ሳይሆን በእግዚእብሔር ባሕርይ፣ ፍላጎት፣ መንገድ እና ክብር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ነው።

መ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ እግዚአብሔር በባሕርያቱ በሆነው መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ነው።

ሠ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ለመንከባከብ፣ በሕይወት፣ በባሕርይ፣ በመገለጥ እና በአገልግሎት እግዚአብሔርን መሆን ያስፈልገናል፦

1. የመለኮታዊው ሕይወት ጥቅል ድምር፣ ብሎም መለኮታዊውን ሕይወት ራሱን እንሆን ዘንድ ሦስታንዱን አምላክ እንደ ምንጭ፣ እንደ ፍልቅ እና እንደ ወንዝ በመደሰት በመለኮታዊው ሕይወት ፈጽመን መሞላት ያስፈልገናል—ዮሐ. 4፥14፤ ቆላ. 3፥4።
2. በፍቅር፣ በብርሃን፣ በጽድቅ እና በቅድስና ባሕርያቱ እግዚአብሔርን መሆን ያስፈልገናል።
3. በእረኝነታችን እኔነትን ከግል ጸባዩ እና ከልዩ ባሕርያቱ ጋር ሳይሆን እግዚአብሔርን እንድንገልጥ የክርስቶስ ርቢ፣ የእግዚአብሔር መገለጥ መሆን ያስፈልገናል።
4. እግዚአብሔር በሆነው ነገር መሠረትና በኢኮኖሚው ባለው ግቡ መሠረት ለመንጋው በሚሰጠው የእረኝነት አገልግሎቱ እግዚአብሔርን ልንሆን ያስፈልገናል።

**VI. የክርስቶስን አካል የሚገነባው እረኝነት የእርስ በርስ እረኝነት ነው—1 ቆሮ. 12፥23-26፦**

ሀ. ሁላችንም ሌሎችን በእረኝነት ለመንከባከብ በክርስቶስ ሕይወታዊ እረኝነት ሥር መሆን እና ከእርሱ ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል—ዮሐ. 21፥15-17።

ለ. የሕይወት እድገት ደረጃቸው ምንም ቢሆን አማኞች ሁሉ እረኝነት ያስፈልጋቸዋል።

ሐ. ሁላችንም እንከኖች እና እጥረቶች አሉን፣ ሌሎች በእረኝነት እንዲንከባከቡንም ያስፈልገናል።

መ. እርስ በርስ የእረኝነት እንክብካቤ የምንሰጥ እና የእረኝነት እንክብካቤን የምንቀበል በጎችም እረኞችም ነን።

ሠ. በዚህ የእርስ በእርስ እረኝነት በኩል፣ አካሉ ራሱን በፍቅር ያንጻል—ኤፌ. 4፥16።

*© 2026 Living Stream Ministry*